እንደምን ሰነበታችሁ ፍኖተዎች

ይህችን ደብዳቤ እንድጽፍ ያነሳሳኝ ከሰሞኑ በአንድ የኢህአፓን ታሪክ ያጠቆረ እየመሰለው ያገኘውን ሁሉ በመለጠፍ የሚታወቅና በአማራው ስም ዘወትር መመጽደቂያ የሆነ ድህረ ገጽ ላይ እንደተለመደው ያለምንም ማመሳከሪያ እንደወረደ የለጠፈውን "ኢህአፓ ለምን ተከፈለ? ዛሬስ ምን መደረግ አለበት?" በሚል ርዕስ አንድ የድርጅቱን ጉባዔ ረግጦ የወጣ አንጃ በዘፈቀደ የቀበጣጠረውን ጽሁፍ በመመልከቴ ነው፡፡

ውድ ፍኖተዎች፣

እንደሚታወቀው ኢህአፓ በኒያ ኢትዮጵያ አሉኝ ባለቻችው አገር ወዳድና አርቆ አሳቢ ትውልድ ለአገርና ለወገን ብሩህ ተስፋና ታላቅ ራዕይ ሰንቀው፣ ትግሉ የሚጠይቀውን መስዋዕት ሁሉ ከፍለው አገራቸው ወደፊት እንዳትሄድ ለአምስት አሰርተ ዓመታት ኮድኩዶ ካሰራት ባላባታዊ (ፊውዳላዊ) ስርዓት ተላቃ፣ ህዝብ የሀገሩ ባለቤት፣ የስልጣኑ ምንጭ የወደፊት እጣው ወሳኝ የሚሆንበት ህዝባዊ መንግስት ተቋቁሞ የፈጣን እድገትና ስልጣኔ በር የምትከፍት ኢትዮጵያን እውን ማድረግ ነበር፡፡ በመቶ ሺዎች የሚቆጠር ዓባላቱም ለሀገር ሉአላዊነትና ለወገን ነጻነት ውድ ህይወታቸውን ሰውተዋል፡፡ ሆኖም በዚህ ግማሽ ምዕተ ዓመት ባስቆጠረ ታላቅ የትግል ጉዞ ድርጅቱን ካጋጠሙት ብዙ ዘርፈ ብዙ ችግሮች ውስጥ፣ ምናልባት አጅግ አስቸጋሪ የሆነው ከአባላቱ መካከል ተስፋ የቆርጡና ጨለምተኛ የሆኑ ጥቂቶች ቡድን ፈጥረው እጅ የመስጠት ፍላጎታቸውን በተቆርቋሪነት ሽፋን ድርጅቱን ለመበተን የሚነሱትና ይህ ዓላማቸው ሲከሽፍባቸው ከጠላት ጋር በሚስጥር ተሞዳሙደው ልክ ወደ ካንሰር እንደተለወጠ እባጭ ድርጅታዊ ሰውነትን የሚያዳክሙት ሁለት ሶስት ጊዜ የተከሰቱ የአንጃ (ፋክሽን) ጥቃቶች ናቸው ማለት ይቻላል ፡፡

ስብጥራቸው አንድ አይነት ባይሆንም ቀንደኞቹ ፓርቲው በአቋራጭ የመንግስት ስልጣን ጨብጦ ወንበር ሲይዙ የሚታያቸው ደካሞች ፣ ትግሉ ገና ብዙ ፈተና፣ መስዋዕትነትና ረዥም ጉዞን የሚጠይቅ መሆኑን ሲረዱ ተስፋ ቆርጠው ሽብረክ ሲሉ፣ በቀላሉ ዋና ጠላት የሚያደርጉት በአላማው ጸንቶ የቆመውን ክፍል ነው ፡፡በአንድ ወቅት አምነው ለቆሙለት ዓላም ብቻ ሳይሆን ለራሳቸውም ክብር አጥተው፣ ያን አክ አንትፍ ያሉት አገዛዝ ጫማ ስር ይወድቃሉ፡፡ የቀድሞ አቋማቸውን የሚያስታውሳቸውን ሁሉ አምርረው ከመጥላታቸው የተነሳ ድርጅቱንና አባላቱን ከጠላት ጋር አብረው ያሳድዳሉ፡፡ የፕሮፖጋንዳው ወናፍም ይሆናሉ፡፡ አሁን እያደረጉ እንዳሉትም ከአምባገነን አገዛዞች ጋር ተባብረው ከማዋከብ ጀምሮ ረግጠው የወጡትን ድርጅት ስም ነጥቀው የጥቅማ ጥቅም መለዋወጫም ያደርጉታል፡፡ በደም ከተጨማለቀው ፋሽስታዊ አገዛዝ አስከ ወያኔ ከተባለው መርገም እና ከጡት ልጆቹ አወሊያዊ ዘረኞች ተባብረው ይዘምቱበታል፡፡ ህብረተሰቡንም ኢህአፓ ለሁለት ተከፈለ ከማለትም አልፈው ኢህአፓ አገር ገባ በሚል በማወናበድ የአገዛዙን እድሜ ያራዝማሉ የህዝብን ትግልም ያዳክማሉ፡፡

ውድ ፍኖተዎች

በዚች አጭር ደብዳቤየ ማስተላለፍ የፈለኩት መልክት አንጃ የሚለውን በድርጅት ውስጥ ቡድን ፈጥሮ የሚነሳ ክፍል (ክሊክ) አነሳስ፣ ስብጥርና አካሄድ የሚመለከት ሳይሆን፣ በኢህአፓ ውስጥ ከተፈጠሩ ብልሹዎች መካከል አንዱ የሆነውና በፈረንጆቹ 2007 ዓ ም የተካሄደውን የኢህአፓ ጉባኤ ረግጦ የወጣውን ቡድን ተከትሎ ለመውጣቱ ይቅርታ ሳይጠይቅ፣ ከ13 ዓመት በኋላ የኢህአፓን አመራር በቅራኔ አያያዝ ድክመት ሲከስ መስማት በነዚህ ጥቂት በማይባሉ ዓመታት ይህ ግለሰብ ከድርጅቱ ብቻ ሳይሆን

ራሱንም ከመጠየቅ ሸሽቶ እንደቆየ አመላካች ነው:: በኢህአፓ ደንብ፣ ጉባኤ ሲጀመር የአመራር ኮሚቴ ዓባላቱ በሙሉ አገልግሎታቸውን ጨርሰው ከስልጣናቸው ወርደዋል:: መጭውን የአመራር የሚያስመርጥ ኮሚቴም ያኔውን ይቋቋማል:: ስለሆነም ሙሉ ስልጣን የሚኖረው አጠቃላይ የአባላቱ ጉባኤ እንጅ ይህ ግለሰብ አንደሚወሸከተው መድረኩ ሁለት አባውራዎች ጎራ ለይተው ፍልሚያ የሚያደርጉበት የቡጢ ቀለበት አይደለም:: ኢህአፓን አንቱ የሚባሉ ግለሰቦች እንደፈለጉ የሚነዱት አድርጎ ለማሳየት መሞከሩም አጅግ የወረደ ጥምቀተ ወያኔ ከመሆን አያልፍም:: በአስራዎቹ የሚቆጠሩ አመራር ኮሚቴ አባላትና በአማካኝ ከ 40 ዓመት በላይ የትግል ተመክሮ ላላቸው ብዙሃን አባላቱ ብቃት ቅንጣት ታክል እንኳን ክብር ቢኖረው እንዲህ ዘቅጦ ድርጅቱን ሁለት ሰዎች ባፈተቱ የሚከፍቱትና የሚዘጉት ሊያደርግ ባልሞከረ ነበር:: ይኸው ነበርኩ ባይ "ያ ትውልድ ተቋም" መሥረትኩ በሚል የሚመጻደቀውም የግል ክፍተቱን የሞላ መስሎት ካልሆነ ላለፉትም ሆነ ለቀሩት ክብር ያለው ግለሰብ ሆኖ እንዳልሆነ ይህ ድርጊቱ ይመሰክራል::

ይህንኑ ተመሳሳይ የማጣጣል ዘመቻ የሸጠ መስሎት ራሱን ከዚህም ከዛም የለሁበትም በሚል የሚቀባጥረው ግለሰብ ጉባኤ ረግጦ ከመውጣቱ በፊት ለተወሰነ ጊዜ በኢህአፓ ስር ወጣቶችን ለማሰባሰባስ በተቋቋመ ጊዜያዊ ኮሚቴ ውስጥ በአስተባባሪ ዓባልነት ተመድቦ በሚሰራበት ወቅት የሚሰባሰበው "ወጣት ከኢህአፓ ጋር ምንም ግንኙነት ማድረግ የለበትም " የሚል አፍራሽ አቋም ይዞ ይገፋ የነበረ መሆኑ ይታወቃል:: በዛን ውቅት ድርጅቱን ከውስጥ ሲያሽመደምዱ ከነበሩትና በኋላ አንጃ ፈጥረው ከወጡ ጋር ሆኖ አንዲሁ በመቀበጣጠር ተባባሪ የነበረና አሁንም የዚሁ የከፋፋይ ዘመቻ ቅሪት የሆነ ግለሰብ ኢህአፓ ለሁለት ተከፈለ የሚል የፈጠራ ትርክቱን ርዕስ አድርጎ የሰለቸ ብረዛውን ከሁለቱም አይደለሁም በሚል ተራ ቅጥፈት መጀመሩም ለዚሁ ነው::

በመጀመሪያ ኢህአፓ ለሁለት ተከፈለ የሚለውን ትርክት መድረክ ረግጦ የወጣው ቡድን ሆን ብሎ ሽንፈቱን ላለመቀበል የመረጠው የተለመደ የማወናበጃ ቋንቋ ነው:: ድርጅቱ ለሁለት ተከፈለ የሚለን ጉባኤው የተጠራበትን ጉዳዮች ተወያይቶ ድምጽ ባልሰጠበትና ገና ወደ ዋና ጉዳዩ ከመግባቱ በፊት መድረኩን ረግጦ እንደወጣ እየታወቀ በየትኛው አካሄድ ነው ባልተወያየበትና ባልተሰጠ ድምጽ አንድ ጉባኤ ለሁለት ተከፈለ የሚባለው? ስለዚህ ድርጅቱ ለሁለት ተከፈለ የሚለው የተለመደ ተራ የፈጠራ ወሬ ነው :: አንዲያውም በአንጃው አንቅስቃሴ ዋና የነበረውና በኋላም " ዛሬ ገና ጠቅላይ ሚኒስቴሬን አገኘሁ" በሚል ለወያኔ ኮሎኔል የሰገደው አዛውንት በዋሽንግተን ሰዓት ከሌሊቱ ሶስት ሰዓት (3:00 AM EST) ላይ ነበር ሆቴሉን ለቆ የወጣው:: ይኸው ለሁለት ተከፈለ የሚለን ግለሰብ ሌላ ያካሄደው ጉባኤ ከሌለ በስተቀር በዚህ ጉባኤ ላይ " ለሁለት ተከፈለ" የሚለው ትርክት ውሃ የሚቋጥርበት አንዳችም ነገር ሊኖር አይችልም:: አንድ ክፍል ተስማምቶ የፈጠረውን ዴሞክራሲያዊ መድረክ (ጉባኤ) የፈቀደለትን መብት ተጠቅሞ ጸንቶ በሃሳብ ከመታገል ይልቅ ጉባኤው ስራውን ከመጀመሩ በፊት ረግጦ ከወጣ ተከፈለ ሳይሆን "አፈርኩ" ብሎ ከዕውነታው ሸሸ ነው የሚባለው:: በተጨማሪም ጉባኤን ረግጦ በመውጣቱ የዚህ ድርጅት አባል እያለ የነበረውን መብት፣ በድርጅቱ ስም የመናገርም ሆነ ቀደም ሲል የነበረው ማንኛውም ቁርኝት ማጣትም እንደሆነ ልብ ይሏል:: ከዚህ ውጭ የሚደመጠው ጫጫታ የፖለቲካ ዘላንነትን እንደ በጎ ምግባር ከማራመድ በስተቀር ሌላ የተሻለ ትርጉም ሊሰጠው አይችልም :: ስለሆነም ምልዓተ ጉባኤው በዋና ዋና አጀንዳዎቹ ላይ ገና ሳይወያይና ድምጽ የመስጠት ደረጃ ሳይደርስ የተወሰኑ ጥቂት ግለሰቦች ረግጠው በመውጣታቸው ድርጅቱ ለሁለት ተከፈለ ብሎ ዲስኩር ማስደመጥ ሃሳዊ ምስክርነት ነው የሚባለውም ለዚህ ነው:: ጉባኤ ረግጦ የወጣውን አንጃ እና ጉባኤውን ጨርሶ ድርጅቱን ያስቀጠልውን

በቁጥር እኩል በኩል ነው በሚል ሊቀላምድም ሞክሯል፡፡ ሃቁ ግን ጥለው የወጡት ግለሰቦች ከ 25 አይበልጡም።

ኢህአፓ አገራዊ ፖሊሲዎችና መተከሎች ዙሪያ ተደራጅቶ የሚታገልና የሚያታግል፣ በህግኛ ደንብ የሚመራ ነባር የፖለቲካ ፓርቲ፣ ከፓርቲም አልፎ እንደ አንድ ብሄራዊ ተቋም የሚታይ ድርጅት እንጅ፣ ነበርኩ ባዩ ሁሉ ድርሻ የሚጠይቅበት የአክሲዮን ማህበር አይደለም፡፡ ፓርቲው ወዳጅና ጠላቱን የሚለየው በመርህ ደረጃ እንጅ በአለፈ ትዝታ አለመሆኑንም መረዳት ግድ ይላል፡፡ ሃፍረተቢስ አንጃዎች ኢህአፓ ለሁለት ተከፈለ የሚለውን ልብ ወለድ ትርክት የመረጡበት ምክንያት ፓርቲውን ተደማጭነት ያሳጡና የዘረኛውን አገዛዝ ለማጠናከር የጠቀሙ መስሏቸው ነው፡፡

ይህ ግለሰብ በዚሁ ከሀቅ የተጣላ አምታች ጽሁፉ አራተኛ ገጽ ላይ በሦሥተኛው ጉባኤ ላይ አንግባ ያሉ አሁን ከገባው "የአቶ እከሌ" ጋር የሆኑና እንግባ ያሉ ደግሞ አሁን ካልገባው "የአቶ እከሌ" ወገን እንደነበሩ ያውቃሉን? በሚል ለአሁኗ አገዛዙን ለማጠናከረ ወደ አገር የገባው አንጃ ቡድን መሪ በጥያቄ መልክ ያስቀምጣል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ይህም እንደተለመደው ተራ ቅጥፈት ነው፡፡ ምክያቱም እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ2001 ተደርጎ በነበረው የድርጅቱ ሦሥተኛው ጉባኤ እንግባ/አንግባ የሚል ጥያቄ ወይም ከዚህ ጉዳይ ጋር እንኳን የሚዛመድ ጉዳይ ጨርሶ ያልተነሳ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የአንጃ መሪዋ እንኳን መደበቅ ያልቻለችውን ሃቅ "ልዩነቱ እንግባ/አንግባ በሚል ነው በማለቷ' የቅርብ ወዳጁን ሳይቀር በየዋህነት የከሰሳት ጉዳይ የተነሳው እአአ በ 2006 ላይ የተካሄደው የድርጅቱ አራተኛ ጉባዔ ከመካሄዱ ከጥቂት ወራት በፊት ነው፡፡ ለወያኔ አፊዳቪት (የቃል ኪዳን) ሰነድ ፈርመን አገር ውስጥ እጅ ሰጥተን እንቀሳቀስ የሚለው የአንጃው አቋም መጀመሪያ በአመራር ውስጥ ቀጥሎ በአባላት ደረጃ በከፍተኛ ድምጽ ብልጫ መሸነፉ ግልጽ ነው። የድርጅቱ አራተኛ ጉባዔም ድርጅቱ በወያኔ ላይ እያካሄደ ያለውን ሁለገብ ትግል አጠናክሮ እንዲቀጥል መመሪያ ሰጥቷል። ከጉባዔው በኋላ አፊዳቪት ፈርመን እንግባ ያለው አናሳ ቡድን የቡዙሃኑ ድምጽ ስላልተዋጠለት የተለያዩ ችግሮችን በመፍጠር የድርጅቱን እንቅስቃሴ በማወኩ አስቸኳይ ጉባዔ እንዲጠራ ምክንያት ከመሆኑም በላይ ግለሰቦች ጉባዔውን ረግጠው ወጥተው የራሳቸውን አንጃ ቡድን ማቋቋም ችለዋል። አንጃው ከድርጅቱ የተለየው የቃል ኪዳን ሰነድ ፈርመን እንግባ በሚል አቋም መሆኑ የሚያከራክር አይደለም። ግለሰቦቹ ከድርጅቱ ተለይተው አንጃ የፈጠሩበት መሰረታዊ ምክንያት አፈዳቪት ፈርመን እንግባ ወይስ ትግላችንን እንቀጥል በሚሉት አቋሞች መካከል መሰረታዊ የሆነ መፍትሄ ባለመገኘቱ ነው በማለት ከአንጃው ቡድን መካከል አንደኛው በጻፈው መጽሀፍ ላይ መገለጹ የሀሳቡን እውነተኛነት ያረጋግጣል። በጊዜው አፊዳቪት ፈርመን አንግባ የሚለውን የደገፉ አመራር ዓባላት ቁጥር ጥቂት ቢሆንም አመራሩ ፈቅዶላቸው ባለ 32 ገጽ መከራከሪያ ሰነዳቸው ወደ ዓባላት ወርዷል፡፡ ዓባላቱም ተወያይተውበት ብዙሃኑ የድርጅቱ ዓባላት ውድቅ አንዳረጉት አየታወቀ፣ የዚህ ግለሰብ ይህንንም ሳያፈር ይክዳል፡፡በእውነቱ የዚህ ግለሰብ ኢህአፓነት ልክ የተስፋየ ገብረአብን (የሻዕቢያው ሰላይ) የኦሮሞነት ሺሙጥ ይመስላል፡፡

"አቶ እከሌና አቶ እከሌ" በሚመሩት ቡድን መካከል የመስመር ልዩነት የለም ይላል (ገጽ 6)፡፡ ማለትም የድርጅቱን ስምና አርማ ሰርቆ ወደ አገር በገባው አንጃና በህቡዕ ትግሉን በቀጠለው ኢህአፓ መካከል ልዩነት የለም፣ ስለሆነም ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ለአረመኔው አገዛዝ ገብቶ "መደመር" የመርህ ወይም የዓላማ ልዩነት አይደለም እያለን ነው ማለት ነው፡፡ በኢህአፓ ውስጥ የተከሰተው የአንጃ ቡድኖች ሁሉ አንድ መለያቸው ሁሉም አክ እንትፍ ብለው የተፉት አገዛዝ ሄደው ጫማው ስር መውደቃቸው ሳያንስ

ትክክለኛዎቹ ኢህአፓዎች እኛ ነን ማለታቸው ነው፡፡ሌላው አይነተኛ መለያቸው ደግሞ ሁሉም የድርጅቱን አመራር በመክሰስ ያታወቃሉ፡፡ ይህንንም የሚያደርጉት ያለ ምክንያት አይደለም፡፡ ዓባላቱን ከአመራሩ በመከፋፈል የቀሩትን ወደነሱ የክህደት ጉዞ እንዲቀላቀሉና ፓርቲውን ለማፍረስ ካልተቻለም ለማዳከም ባላቸው ዓላማ ነው፡፡ ኢህአፓን አስከ አንገታቸው ከታጠቁ ጠላቶቹ ይልቅ ከውስጡ ብልሹ ሆነው የወጡ አንጃዎች ለጠላት መሳሪያ በመሆን ይበልጥ ጎድተውታል፡፡ለዚህም ነው የአሁኖቹ ደግሞ ልክ እንደ ፎረም 84ቶቹ ቀደም ከህዲዎች እኛ ነን ኢህአፓ ብለው ወገንን በመንጋ እያሸበረ ላለው ዘረኛና አረመኔ ቡድን የፖለቲካ ምህዳሩን ሰፍቷል በሚል ሰበብ ሄደው መናጆ የሆኑት፡፡

ይህ በታኝ ግለሰብ አለቆቹን ለማስደሰት፣ አጅ አንሰጥም ብሎ ትግሉን ያስቀጠለውን ኢህአፓና መላ ዓባላቱን የአንድ ነባር ዓመራር ዓባል ጭፍራ ሊያደርግ ይሞክሯል፡፡ ይህ ደግሞ የየትኞቹ ጸረ ኢህአፓ ሃይሎች የፕሮፖጋንዳ ምንጭ እንደሆነ አያውቁብኝም ብሎ ከሆነ ማንንም ሳይሆን ራሱን ነው ያጃጃለው፡፡ ቀጥሎም "ኢህአፓ ለፖለቲካ ትግል ከመቸኮሉ በፊት ገጽታውን ማጽዳት ይገባዋል" ይለናል፡፡ ገጽታውን የሚያጸዳው በእንዶድ ነው በሳሙና አንዳንል ጉዳዩ የሚያስቅ አይደለም፡፡ ኢህአፓ የሀገር ሀብት ዘርፎ ነው? በከርቸሌውና በጉድጓድ እስር ቤቶቹ ዜጎችን አስሮ አሰቃይቶ ነው? አደንዛዥ ዕጽ ሲያዘዋውር ተይዞ ነው? ስለዚህ ይህ አብሪቱ ከችሎታው በላይ የጦዘ ግለሰብ ኢህአፓ ለፖለቲካው ትግል ከመቸኮሉ ገጽታውን ያጽዳ ሲል፣ ፖለቲካውን ለፊንፊኔዎቹ ተውላቸው ማለቱ ነው፡፡ ወይስ በትግል 50 ዓመት እያስቆጠረ ያለውን ድርጅት፣ ወያኔና ደርግ ገጽታህን አጥፍተውታልና ለፖለቲካው አትቸኩል አያለ የረቀቀ ምክሩን የለገሠው? ይህ እጅግ የተንደገደገ ግለሰብ በዚህ አላቆመም የተለመድ ከፋፋይና በታኝ ተልዕኮውን ይበልጥ ግልጽ የሚያደርገው በገጽ 8 " የትኞቹንም ኢህአፓ ሳያካትት ሙሉ በሙሉ የሀገር ቤት ኢህአፓዎች ብቻ ራሳችሁን አደራጅታችሁ የሀገርቤቱን ኢህአፓ አጠናክራችሁ ቀጥሉ " ይላል፡፡ ቀደም ሲል ለመጠቆም እንደሞከርኩት ከድርጅቱ አንጃ ሆኖ ከመውጣቱ በፊት የኢህአፓ የወጣት ክንፍ ድርጅት ወክንድን ከፓርቲው ለመነጠል ወጣቱ ከኢህአፓ ጋር ምንም አይነት ግንኙነት ማድረግ የለበትም በሚል ወጣቱን ለመበተን መንቀሳቀሱን ልብ ይሏል፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ በዚህ ዙሪያ ስለግለሰቡ ብዙ ማለት ማለት ቢቻልም በአጠቃላይ ተልዕኮው ግን የመሠረታዊ ለውጥ ጥያቄ ይዞ የሚንቀሳቀሰውን ኢህ አፓ ለማዳከም አይነተኛ መሳሪያ አርጎ መጠቀም የሚቻለው እንዲህ አይነቶቹን ነበርን ባይ አምታቾችን በመጠቀም ነውና፣ በትግሉ የተሰውትን ሰማዕት ስም በመጠቀም ትግሉን ያስቀጠሉትን ከማጥቃት ወድኋላ የማይሉ ሃይሎች እንደማይተኙልን መጠራጠሩ ተገቢ ነው ፡፡

ኢህአፓ ሲመሰረት በአገር ውስጥ ተመክሮ ለመውሰድ የሚችልበት ቀደም ብሎ የተቋቋመ የፖለቲካ ፓርቲ ባልታየባት ኢትዮጵያ ሀ ብሎ የጀመረ ድርጅት በመሆኑ በጊዜው በሌሎች አገሮች ከተከሰቱ ህዝባዊ አመጾች፣ የነጻነት እንቅስቃሴዎችና እንዲሁም ከራሱ ልምድ ለመማር ቆርጦና ታጥቆ የተነሳ ድርጅት ነው፡፡ በዋናነት ደግሞ በጊዜው የነበሩትን የኢትዮጵያ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች በተጨባጭና በጥልቀት የመረመረ ለመሆኑም ምስክር የሚያስፈልገው አይደለም፡፡ አሌ የሚል ካለም ያኔ ያነሳቸውና ታግሎ ያታገለባቸው መሠረታዊ ጥያቄዎች እስከዛሬ ድረስ ህያው ሆነው ቀጥለው ሌላው ቀርቶ ትውልዱን የሚፈሩና የሚያጥላሉ አድር ባይ ቡድኖችና ግለሰቦች ሳይቀሩ መሸከም ተገደዋል፡

በመጨረሻ የምለው ቢኖር፡ ኢህአፓ ትውልድን ከአጽናፍ አጽናፍ ያንቀሳቀሰና በሙቶ ሺዎች የተሰውለት ዘመናዊ የፖለቲካ ፓርቲ ነው፡፡ ጠላት አምርሮ የሚጠላውና ከማጥቃት የማይመለሰውም በጦር ሃይሉ

ነው ባልልም በቆመለት ዓላማ፣ ከሕዝብ ወገንተኛነቱና አይበገሬነቱ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በዚህም የዓላማ ግልጽነቱ፣ ጥራትና ጽናቱ ለህልውናቸው ስጋት በመፍጠሩ አምባገነኖችና ብልሹ ጭፍሮቻቸው ዘምተውበታል፤ ከምዕራባዊያን እስከ አረቦቹ ፣ ከተገንጣይ ሃይሎች እስከ ወታደራዊ ጁንታው (ሱዳን፣ ግብጽ፣ አሜሪካ ውዘተ)፣ አንጃዎችና ሆዳም ምሁራን ምላስና ብዕሮቻቸውን ቀስረውበታል፡፡ ከጸረ ኢትዮጵያ ጠባብ ብሄረተኞች፣ አንጃዎችና ሆዳም ምሁራን የሰማነውን የፈጠራ ወሬ መልሰን ከማስተጋባት ይልቅ የቡድን ግርዶሽን ቀዶ ትልቁን ስዕል ማየት የሚችል ኢትዮጵያዊ ዜጋ "ለምን ይሆን በኢህአፓ ላይ እነዚህ ሁሉ የውስጥና የውጭ ሃይሎች የሚረባረቡበት? ብሎ ቢጠይቅ መልሱ ከባድ አይሆንም ነበር፡፡ ይህን ባለመጠየቅም ነው ብዙዎች ጠላትን ከወዳጅ መለየት ተስኗቸው እንደ ሀረግሬሳ ከመጣው አፈጮሌ ላይ ፈጥነን በመጠምጠም ታሪክ ይቅር በማይለው ተደጋጋሚ ስህተት ዘረኛው አገዛዝ ህዝብን ንቆ አገር እያፈረሰ፣ መሬቱን ለቁሮ ጀሌዎቹ እያከፋፈለ፣ ህዝብን ከቀየው እያፋለሰ ብልጽግኛ ነው አትጠይቁን ግን ተቀላቀሉን ለማለት የደፈረው ፡፡ መፍትሄው እየተደራጁ መታገል፣ እየታገሉ መደራጀት ሲሆን፣ ድምጻችን ደግሞ ...

ምርጫ የሚለው የዘረኞች ቀልድ ይቁም!
ሁሉን አሳታፊ የሽግግር ሂደት አሁኑኑ ይጀመር!!

እያዩ መንገሻ

ከማድሰን ዊስኮንሰን
ሰሜን አሜሪካ